# <u>አንጃ ሁሌም አፍራሽ ነው</u>

**ጀምበር ደግፌ**

**እነኚህ ኢሕአፖች ስም ማውጣት ያውቃሉ**
**በዚህ ዶክተር ብለው በዚያ ዜሮ ይላሉ፡፡**

የተባለውን ያስታውሷል፡፡ ለነገሩማ ስም ማውጣት ያውቃሉ የተባለው ለበለሴዎች ነበር፡፡ በለሳ ብዙ ጀግንነት የተመዘገበባት ነበረች፡፡ እነ ተፈራ ዋልዋና በጭልጋ አኩርፎ ከጦርነት ርቆ የመሸገው ዶክተር ዜሮ የሚያውቁት ባይሆንም፡፡ ለዚህ ፅሁፍ ያነሳሳኝ ዋና ጉዳይ ግን ዛሬም ከስንት ተመክሮ በኋላ ብዙ ቀና ዜጎች ስለ በታኞችና አንጃዎች ዋና ጠባይ ግንዛቤ ሲያንሳቸው በመታዘቤ ነው፡፡ የኖርዌይ ታዛቢ ለምሳሌ አዛውንቱ የአንጃ መሪ በአደባባይ ዋሽ ብሎ ይገረማል፡፡ ሌሎች ደግሞ የበረከት ስምዖን ወዳጅ ብርሀኑ ነጋ እየሰራ ባለው ሻጥር ሲገረሙ ይታያሉ፡፡ የአንጃና አፍራሾች ጠባይ በሚገባ ከታወቀ ግን መገረም አይኖርም፡፡ መሞኘትም አይከተልም፡፡

**የአሲምባ ጦር ሜዳ በፈሪነት ሲያውቀው**
**ማነው ያን ብርሃኑን ኮማንደሬ ያለው?**

የተባለውም ቢጠቀስ ቦታው ነው፡፡ ማን ማን መሆኑ ከተለየ ቀበሮ በግ ነኝ ሲል ወይም የቡከን ምሳሌ ጀግና ጦረኛ ነኝ ሲል የሚታለል አይኖርም ማለት ነው፡፡ አንጃ የሚፈጠረው በአፍራሾች ነው፡፡ የድርጅትን ህግ በሚጥሱ፣ የብዙሃኑን ውሳኔ መቀበል በሚያዳግታቸው፣  የግል ዝናና ተክለ ሰብ ግንባታ  የተወጠሩ ግለሰቦች የእኔ ፍላጎት ካልተሟላ ድርጅት ይፍረስ ብለው ሲነሱ ነው፡፡ በቅንጅትም በኢሕአፓም የተከሰተው አንጃ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ የኢሕአፓውን በተመለከተ ዕድሜዬ ገፋ፣ደም ብዛት ሊገለኝ ነው፣ ሚኒስቴር እንኳን ሳልሆን ልሞት ነው ወዘተ ብሎ ቅጥ አምባሩ የጠፋው አዛውንትና ጤነኛ ለመሆኑ ገና ማረጋገጫ የሚጠይቅ ሙያተኛ አፍራሽና በታኝ ዶክተር ዜሮ በሚያስገርም ህብረት (ለተንኮል ሆኖ እንጂ አይስማሙምና) ድርጅቱን ለማፍረስ አሲረውና ሰልፋቸው ከወያኔ ሳይሆን አይቀርም የሚባሉ ጀሌዎችን፣ የኢሕአፓን አኩሪ ኢትዮጵያዊነት ጥለው ጎጠኝነትን ያቀፉ ወራዶችን አቅፈው በኢሕአፓ ላይ ዘመቱ፡፡ አዛውንቱም የለፋበት ተንኮል የማይሳካ መሆኑን ሲረዳ በሌሊት ፈርጥጦ መኮብለልና በዚሁም ዘላለማዊ ውርደትን መከናናብ ተገደደ ፡፡ ቅጥፈት ደግሞ የቆየበትና ቤተ የሰራበት ልምዱ ነበርና ባልተገኘበት ሰልፍ ተገኘሁ ብሎ የኖርዌይ ሀገርወዳዶችን ቢያስገርም በበኩሌ አይደንቀኝም፡፡ ኬንያ ሄዶ፣አሰሎ ሄዶ ቅሌቱን ሲቀበል ድል አገኘሁ አላለም? የቀድሞ ጓዶች ስብሰባ በዓይኑ ላይ ባዶ ሲቀር አይደል አያሌዎች ተደሰባሰቡ ብሎ ሲቀጥፍ ሲሰማ የነበረው? ወደ ቅንጅት ስንመለሰ ደግሞ ይህን ሕዝብ አቅፎ ደግፎት የነበረውን ድርጅት ገና ከመጀመሪያው ሊያዳክሙትና ሊጎዱት የተነሱት ራሳቸውን ቀስተዳመና ያሉ በተለየም ብርሀኑ፣አንዳርጋቸውና የፍርሻ ፕሮፌሰሩ መስፍን መሆናቸው የታወቀ ጉዳይ ነው፡፡ ቅንጅት በወያኔ ሲጠቃና ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ህብረት በሚያሻው ጊዜ ብርሀኑ ነጋ ከዚያ የቅሌት ቋት ከበየነ ጴጥሮስ ጋር ሆኖ ና ከእነ በረከት ስምዖን ተመሳጥሮ የሕዝብን ትግል አከሸፈ፣አደናቀፈ፣ ለወያኔ ጠቀመ ፡፡ ብርሃኑ ነጋ ከፈሰሰው ጋረ ፈሶ ኢሕአፓ ሆንኩ ብሎ በከተማ በድንጋጤ ተሸብሮ ወደ አሲምባ ሲላክ ቢዘህ ሜዳ ደግሞ ይህ ነው የማይባል ፍርሀት አሳይቶና በአንጃነትም ተሰማርቶ ያካበተው የክህደት ታሪክ ነበረውና ለሚያውቁት ክህደቱ አላስገረመም፡፡ የኢሕአፓው ዶከተር ዜሮ ዓይነት፡፡ ሞት ለኢሕአፓ መሪዎች ያለ በታኝን ዳግም አቅፈው ለአመራር ቦታ ያበቁት መጠየቅ አለባቸው፡፡ ብርሃኑም ከወያኔ ጋር ያን ሁሉ ዓመት አሳልፎ ሳለ የሕዝብ ድርጅት መሪ ብለው የተቀበሉት ቢጠየቁ አግባብ ያለው ነው፡፡ ንስሐ ያልገባን ከህዲ ማግበስበሱ በመጨረሻ ውጤቱ መጥፎ ለመሆኑ ማስረጃ ለሚጠይቁ መልሱ ግልፅ ሆኗል፡፡

አንጃ ሁሌም ሲፈለፈል ለሕዝብና ለትግል ቀና ያሰበ መስሎ ነው፡፡ እነ ዶክተር ዜሮ ሰራዊት ሲበትኑ የለም በተጠናከረ መንገድ ልንታገል ነው ብለው ነበር በመጀመሪያ፡፡ ግን ሰራዊቱን ለሱዳን ሲያበቁና የሰራዊቱን መሳሪያ ለሱዳን ሲያስረክቡ ይህ ልፈፉቸው ሀሰት መሆኑ

ተጋልጧል፡፡ ዶክተሩም ሞት ለኢሕአፓ አመራር ብሎ ሲደፍቅና ሲያጓራ እሰይ ያለው አሜሪካ ተቀብሎ ለአሜሪካና ለትምህርት አብቅቶታል፡፡ አዛውንቱም ቀውስና ከባድ ሁኔታ በመጣ ቁጥር ትግል እናቁም እያለ ሲርበተበት ተው ብለው ያገዱትን (ግን ገበናውን የደበቁለትን) ዛሬ ቢያወግዝ የሚገርም አይሆንም፡፡ ጥሉ ከሀፍረቱ ጋር ነው ሀቁ ይነገር ከተባለ፡፡ የቅንጅቱ አንጃም ቢሆን ይህንን ድርጅት ለማፍረስ ደፋ ቀና ሲል ቆይቶ በተለይም ዋና ደንቃራ የተባሉትን ኤንጂነር ሀይሉ ላይ ዘምቶ የተሰጠውን ከይሲ ተልዕኮ ሊያሟላ ከሞከረ በኋላ ይህ ደግሞ በተወሰነ ደረጃ (በወይዘሪት ብርቱካን በኩል) ከተሳካ በኋላ በልዩ ተልዕኮ ደረጃ በትጥቅ ትግል የሚሰማሩትንና ሊሰማሩ ያሰቡትንም ለማደናቀፍ በአዲስ መልክ ተቃኝቶ ስራ ጀምሯል፡፡ ባሩድ ሳይሸተው መሬት የሚከዳው ብርሀኑ ነጋ ዛሬ   የሁለገብ ትግል (ከኢሕአፓ የተወሰደ ነው!) አባወራ ነኝ ሲልና ምናልባትም  ወኔ በከዳው አዛውንትና ዶክተር ዜሮ ተደግፎ ቢነሳ መለስ ዜናዊ ብርክ ይዞት ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ ለድርድር ሲመጣ የሚታያቸው ማፈሪያዎቹ አንጃዎች ብቻ ናቸው፡፡ መለስ ዜናዊ ድንጉጥ ነው   ቢባልም ፈሪና ጀግናን መለየት የሚያቅተው ባለመሆኑ በአይጋ ፎረም ድህረ  ገፅ እንደሚታየው  በኮማንደር ብርሃኑና  በብተናው ሻለቃ የሚታወጅ ሁለገብ ትግል (ሲባል ተሰምቶ!) ሊያስደነግጠው አይችልም፡፡ በፈሪ ዶክተሮች ዜሮ ጦር እወጃ ጫቱን እያቃመ ቂቂቂቂ በማለት ላይ ነው፡፡

አንጃዎች ስራቸው ጠላት በተባለው ስርዓት ላይ መዝመት ሳይሆን በታጋይ ድርጅት ላይ ዘመቻ ማካሄድ ነው፡፡ በአንጃነት ሲሰማሩ በመሰረቱ ከሕዝብ ጠላት ጋር በይፋም በድብቅም ለመተቃቀፍ ነውና ዋና ጠላት ብለው ሊያጠፉ የሚነሱት የነበሩበትን ድርጅት ነው፡፡ እስቲ በተጨባጭ እንየው፡፡ የኢሕአፓ አንጃ ብቅ ካለ ጊዜ ጀምሮ በየፓልቶኩና በየቃለ መጠይቁ እየዘመተ ያለው በኢሕአፓና በዚህ ድርጅት ፅኑ መሪዎች ላይ ነው፡፡ ይህን ዘመቻ ለማሟላት አዛውንቱና ዜሮ ከቀይ ሽብር ወንጀለኞች ጎራ መግባት ብቻ ሳይሆን ድርጅቱን ይጎዳል ያሉትን ሀሰትና  ምስጢር ሳይቀር በአደባባይ ረጭተዋል፡፡አመመኝ ደከመኝ ይል የነበረውም አዛውንት ከአሜሪካ ናይሮቢ፣ ከኬንያ ኖርዌይ ከዚያም ካናዳ ከዚያም ቺካጎ ከዚያም ዳግም ኖርዌይ እየበረረና ሀሰቱን እየረጨ በመራወጥ ላይ ነው፡፡ ለድርጅታቸው ሲሆን ወገቤን ያሉት ገንዘብም ዛሬ ለጥፋት ተልዕኮአቸው ተትረፍርፏል (ወይስ አያ ወያኔ ነው ከፋዩ?)፡፡ ዘመቻቸው ወያኔን ጠላት ብሎ መዋጋቱ ሳይሆን ኢሕአፓን በጠላትንት ፈርጆ ማደናቀፉና ማጥቃቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የአንጃዎች ዋና ጠባይና መለያ ነው፡፡ ሞት ለኢሕአፓ አመራር ያለው በታኝ ሞት ለፋሺስቱ ደርግ ሲል ያኔም አልተደመጠም ነበር-- ዛሬም ያው ነው፡፡ ወያኔን በማውገዝ ፈንታ ኢሕአፓን መቀጥቀጡን መርጠዋል፡፡ ይህን  ለማድረግ ደግሞ ዝቅጠት ዕጣዬ ብለው ወደ ጎጠኝነትም መውረዳቸው የሚታይ ነው፡፡ ኢንጂነር ኃይሉ ላይ የተካሄደው ዘመቻ፣ ዶክተር ታዬ ላይ የተወረወረው ፀያፍ ጦር ሁሉ ሌላ የሚጠቀሰ  ነው፡፡ አንጃው በወያኔ ላይ ሳይሆን ሕዝብ በደገፈው ቅንጅትና መሪዎቹ ላይ ዘምቷል፡፡ አሁንም አላቆመም፡፡ በባዕዳንም በዚሁ እየተረዳ መሆኑ ለኢንጂነር ኃይሉ ቪዛ በከለከለችው ካናዳ ተጋልጧል፡፡ ዛሬ የእነ ብርሀኑ ትጥቅ ትግል እወጃ ቀልድ ለመሆኑ ከራሱ ከሰውየው ገለጣዎችም መረዳት የሚቻል ነው፡፡ በትጥቅ ትግል ወያኔን እናስወግዳለን በሚል ፅኑ አቅዋም ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ወያኔን ወደ ድርድር ለማምጣት በሚል የተቃኘ ነው፡፡ የፈሪ ዱላ እንኳን ሊባል አይችልም፡፡  የእነ ብርሃኑ ዋና አላማ ትጥቅ ትግል የሚሉትን ማደናቀፍ ነው፡፡ በሻጥሩ ደግሞ ወያኔ የለበትም ማለት አይቻልም፡፡ ኮማንደር ብርሃኑ ከወያኔም ከአሜሪካም ጡት ከተጣቡ ቆይቷልና፡፡

እነ ዶክተር ዜሮ ድርጅት ሊያፈርሱ

ገትጋታው አዛውንት አንጃነት ሊያነግሱ

ኮማንደር ብርሃኑ ጦርነት ሊያውጁ

ግም ለግም ተቃቅፈው ወደ ግም ሊጓዙ

በጋራ ቢያድሙ በጋራ ቢነሱ

በሕዝቡ ትግል ላይ ዳግም ሊቀልዱ

ኢትዮጵያ በሞላ አላቸው ወግዱ

የተባለውንም ልንነግራቸው ይገባል::

አንጃነት ክህደት ነው::

አንጃነት ውሎ አድሮ የሚጋለጥ ወያኔነት ነው::

አንጃነት የሕዝብን ትግል የሚፃረር ነው::

ባንዳ አንጃ በታኝ ሁሉም ፀረ ኢትዮጲያነት ነውና ነቅተን እንታገላቸው::